# ሠልፅክተ ሰጠጉ

መጋቢት 2008 ዓ.ም.

በየወሩ የሚወጣ የሰመጉ ልሣን

24ኛ ዓመት ቁጥር 004

## በውስጥ ገጾች

ገጽ 3 በአፍሪካ ስሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተጠያቂነትን ማስፈን

ገጽ 5 ጽንፈኛ ብሔር ተኮር ፖሊቲካና ያልተመለሱ የማንነት ጥያቄዎች

ገጽ 8 የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ቁርጠኛነት ከፓሪስ መርሖዎች አንፃር

ገጽ 11 ከምርመራ ማኅደር

# ርዕሰ አንቀጽ

## የሕዝብ ጥያቄ ይደመጥ!

መንግሥት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ቆርጦ መነሣቱን በተደጋጋሚ በመግለጽ ላይ ይገኛል፡፡ ነገር ግን ከሕዝብ አስተዳደር ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉትን ሥር የሰደዱ ችግሮች ለመፍታት የፖሊቲካ ቁርጠኛነት እንዳለው እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ ሕዝቡ ለሚገጥሙት ችግሮችና ለሚደርሱበት በደሎች መፍትሔ ይሰጠው ዘንድ በሰላማዊ መንገድ ጥያቄውን የማቅረብ ሕገ መንግሥታዊ መብት ቢኖረውም ይህ መብቱ ግን እየተከበረ አለመሆኑ በግልጽ ይስተዋላል፡፡ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 30 የተደነገገው የዜጎች የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት በመንግሥት አካላት ሲጣስ ይስተዋላል፡፡ ምንም እንኳ በሕገ መንግሥታዊው ድንጋጌ መሠረት ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት ቢኖረውም የገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ ቡራኬ ከተሰጣቸው የድጋፍ ሰልፎች በቀር የተቃውሞ ሰልፎችን ማድረግና አቤቱታ ማቅረብ እንደወንጀል እየተቆጠረ የመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች በዜጎች ላይ የሕይወት ማጥፋት፣ የአካል እንዲሁም የሥነ ልቡና ጉዳት ሲያደርሱ ማየት የተለመደ ክስተት ሆኗል፡፡ ተደጋግሞ እንደሚስተዋለው መንግሥት ለሕዝብ ጥያቄ ጆሮ ሰጥቶ ዜጎችን ላማረሩ ችግሮች ተገቢውን መፍትሔ በመስጠት ፋንታ የሚቀርብለትን ጥያቄ ‹‹የጸረ ሰላምና የጸረ ልማት ኃይሎች አጀንዳ ነው›› በሚል ትክክለኛ ያልሆነ ፖሊቲካዊ ምክንያት ጥያቄዎችን ገሸሽ አድርጎ በማለፉ የሕዝቡ ጥያቄ ወደቁጣ ተለውጧል፡፡ ከ2006ዓ.ም አንሥቶ በኦሮሚያ ክልል ሲሆን የተመለከትነውም ይህንኑ ነው፡፡ የአዲስ አበባና የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላን በፊንፊኔ ዙሪያ ባሉ የኦሮሚያ ከተሞችና የገበሬ ማኅበር መንደሮች ማፈናቀል ስለሚፈጥር ማስተር ፕላኑን እንቃወማለን በማለት በኦሮሚያ ክልል ባሉ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች የሚማሩ ተማሪዎች ከሚያዚያ ወር 2006 ዓ.ም ጀምሮ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ አካሂደዋል፡፡ ዳሩ ግን የተማሪዎቹ ጥያቄ ምንም ይሁን ምን በሰላማዊ ሰልፉ ላይ ለተነሡት ጥያቄዎች መንግሥት በሰላማዊ መንገድ መልስ መስጠት ሲገባው ሕገ መንግሥታዊና ዓለም አቀፋዊ አስገዳጅ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ የኃይል እርምጃ በመውሰዱ ዜጎች ለሕገ ወጥ ግድያና እሥር እንዲሁም ለእንግልት ተዳርገዋል፡፡

ዜጎች ሕይወታቸውና ኑሯቸውን በሚመለከቱ የመንግሥት ዕቅዶች፣ ሕጎችና ፖሊሲዎች ላይ የመሳተፍ፣ የመወያየት፣ ሐሳብ የመስጠት፣ የመጠየቅና የመቃወም መብት እንዳላቸው በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ላይ ከመደንገጉ በላይ አሳታፊነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት የመልካም አስተዳደር እና የሰብዓዊ መብቶች መከበር መሠረቶች መሆናቸውም ይታወቃል፡፡ መንግሥት የተቀናጀ የማስተር ፕላኑን በማርቀቅ ኺደት ዜጎችን በተለይም በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ የኦሮሚያ ገጠርና ከተማ ነዋሪዎችን ባለማሳተፉ፤ ከብዙ ደም መፋሰስ በኋላ ‹‹ተግባራዊ አይደረግም›› የተባለውን ረቂቅ ሠነዱንም እስከዛሬ ድረስ ለሕዝብ ይፋ ባለማድረጉ የብዙ ዜጎችን ሕይወት ለቀጠፈውና የአካልና የንብረት ጉዳት ላስከተለው ቀውስ ምክንያት ሆኗል፡፡ ረቂቅ ማስተር ፕላኑ ለባለሙያዎችና ለሌሎችም ባለድርሻ አካላት ቀርቦ ግልጽ ውይይት፣ ክርክር እና ትችት ሊደረግበት ሲገባ ለዓመታት በምሥጢር መያዙና ይዘቱም ለዜጎች አለመገለጹ ለጥርጣሬ፣ ለውዥንብርና ደም ላፋሰሰ ግጭት መንሥዔ ሆኗል፡፡

ስለሆነም መንግሥት ሕዝብ ለሚያቀርበው ጥያቄ በጊዜ አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጥና በኦሮሚያ ክልል ለደረሰው አስከፊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በዋናነት ተጠያቂ የሆኑ የመንግሥት ባለሥልጣናትን፣ የመከለካያ ሠራዊት አባላትን፣ የፌደራልና የኦሮሚያ ፖሊስ አባላትን እንዲሁም የወረዳና የቀበሌ ታጣቂዎችን ለፍረድ አቅርቦ ተጎጂዎች ፍትሕ እንዲያገኙ በማድረግ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ሰመጉ አበክሮ ይጠይቃል፡፡

## የሰመጉ አድራሻ

ዋናው ጽ/ቤት፡ አዲስ አበባ

ኢ.አ ስታዲየም አጠገብ ላሊበላ ሬስቶራንት ጎን፣ ሣኅለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ፣ ቢሮ ቁጥር 19

ስልክ: (+251) 011 551-7704

ፋክስ: (+251) 011 551-7704

ኢሜይል: info@hrco.org.et

ድረ ገጽ: www.hrco.org.et

የፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432

አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ

### የሰብዓዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ መምሪያ

ስልክ: (+251) 011 558-2387

ኢሜይል: monitoringcomplaints@hrco.org.et

### ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

ሐዋሳ (ደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና)፡

ስ.ቁ(+251)046 220-4500፣ ፖ.ሳ.ቁ 360

ባሕርዳር (ሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና)፡

ስ.ቁ(+251)058 220-0240፣ ፖ.ሳ.ቁ 1115

ነቀምቴ (ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና)፡

ስ.ቁ (+251) 057 661-5014፣ ፖ.ሳ.ቁ 463

ድሬደዋ (ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና)፡

ስ.ቁ (+251)025 811 9150 ፖ.ሳ.ቁ 2596

ጅማ (ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና)፡

ስ.ቁ (+251) 147 211 5434

አዲስ አበባ (ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀጠና)፡

ስ.ቁ (+251) 011 551-7704፣ ፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432



### የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት

አቶ ብዙዐየሁ ወንድሙ - ሰብሳቢ

አቶ ዘየደ ገ/ጻዲቅ - አባል

አቶ ዳን ይርጋ - አባል

አቶ ደረጀ መላኩ - አባል

አቶ ሱራፍኤል ግርማ - አባል


# የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)፤ የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ) በኢትዮጵያ የመጀመሪያው መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋም መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሰመጉ ከተቋቋመበት 1984 ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት 24 ዓመታት ሁለንተናዊ ሐገራዊ ተልዕኮ በመያዝ በቀመላቸው ዐበይት ዓላማዎች ላይ በመመርኮዝ በነደፋቸው በርካታ ፕሮግራሞች አማካኝነት የሰብዓዊ መብት መከበር፣ የሕግ የበላይነት እና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲሰፍን በመታገል በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲዳብር የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል፤ እያበረከተም ይገኛል፡፡

ይህን ተልዕኮውን ለማሳካት ሰመጉ ፈርጀ ብዙ የሆኑ መንገዶችን በመጠቀም የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕ እንዲያገኙ፣ የጥሰቱ ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁ፣ የሰብዓዊ መብት ግንዛቤ በሕዝብና በመንግሥት አስፈጻሚ አባላት ዘንድ እንዲዳብር፣ የተፈጸሙ ጥፋቶች እርማት እንዲያገኙ በአጠቃላይም የሕዝቡ ግንዛቤ እንዲዳብር ብዙ ሠርቷል አሁንም በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

ዋና ዋናዎቹ የሰመጉ የሥራ ኃላፊነቶችም፤ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን መከታተልና ለሚመለከታቸው የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በማሳወቅ እንዲታረም ማድረግ፣ የሕግ ድጋፍ መስጠት፣ የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፣ በሰብዓዊ መብቶች ላይ ትምህርት መስጠት፣ የወጡና የሚወጡ ሕጎች በትክክል ስለመተግበራቸው መከታተል፣ የሰብዓዊ መብት አያያዝን መከታተል፣ የሕግ ታራሚዎችን መጎብኘትና ሰብዓዊ መብቶቻቸው መጠበቁን ማረጋገጥ፣ መመርመርና መግለጫ ማውጣት ናቸው፡፡

በእስካሁኑ ቆይታው ሰመጉ 36 መደበኛ መግለጫዎችና 139 ልዩ መግለጫዎችን በተጨማሪም በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይፋ አድርጓል፡፡ ከእነዚህም ባሻገር ሕዝቡ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ለሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ ትግበራ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ለማስቻል ተከታታይ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርት የአድቮኬሲ እና የሕግ ድጋፍ ሥራዎችን አከናውኗል፡፡ አሁን በሚገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም ዐቅም በፈቀደለት መጠን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ካለው የጸና ዓላማ አኳያ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

**ማሳሰቢያ**

**1. መልዕክተ ሰመጉ በአውሮፓ ኅብረት የገንዘብ ድጋፍ የሚታተም የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ /ሰመጉ/ ልሣን ነው፡፡ በልሣኑ ላይ የሚታተሙ ጽሑፎች በጠቅላላ የአውሮፓ ኅብረትን ዐቋም የማያንጸባርቁ መሆናቸውን ሰመጉ ለአንባቢያን ያስታውቃል፡፡**

**2. የሰመጉ ድርጅታዊ ዐቋም የሚገለጸው በርእሰ አንቀጽ ላይ ብቻ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡**

**ሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው!**

HRCO stands for democracy, the rule of law and the respect of human rights



# በአፍሪካ ለሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተጠያቂነትን ማስፈን

## በአሕጉራችን የሚፈጸሙትን መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለመከላከልና የመብት ጥሰት ፈጻሚዎችን ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎችንና እርምጃዎችን ከነውሱንነታቸው <u>የሺህዋስ እሸቴ</u> በተከታዩ ጽሑፍ ይተነትናል፡፡

*መግቢያ፡- ነገሮችን በአንፃራዊ ዕይታ መመልከት*

ማንኛውም ዓይነት የሕግ ጥሰት ሲሆን — ሲሆን ጥሰቱ ዳግመኛ እንዳይከሰት የሚከላከል ቢያንስ ቢያንስ ደግሞ አጥፊው ተጠያቂ የሚሆንበት ተከታይ ውጤት ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት የሕግ ዋና ዋና መለያ ባሕሪያት ከሆኑት መካከል አንዱ የሕግ ተፈጻሚነት አስገዳጅ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ሳይሆን ቢቀር ግን ሕጉ ያላስፈላጊ ክርክር መንሥዔ ይሆንና አስገዳጅ ተፈጻሚነት የሌለው የሥነ ምግባር መመሪያ ብቻ ሆኖ ይቀራል፡፡ ‹‹ሕግ በተፈጥሮው የግዴታ ተፈጻሚነት አለው›› ከሚለው ዕሳቤ የተነሣ በሥነ ሕግ ረገድ ከፍተኛ መሻሻሎች በሚታዩበት በዚህ ዘመን እንኳ ዓለም አቀፍ ሕግ፤ ሕግ መሆን አለመሆኑ ላይ ሙግት የሚገጥሙ ሊቃውንት አሉ፡፡ ዓለም አቀፍ ሕግ በተለያዩ ምድቦች ውስጥ የሚካተቱ ሕግጋት ማዕቀፍ እንደመሆኑ መጠን የዚያ ማዕቀፍ አካላት የሆኑት ነጠላ ሕግጋት በተወሰኑ ወገኖች እንደ ሕግ ሲቆጠሩ በሌሎች ደግሞ እንደ ሕግ እንደማይቆጠሩ መደምደም ይቻላል፡፡ ከዚህም የተነሣ ፈተናው የሚጀምረው ወደ ትክክለኛው አፈጻጸም የሚመራና ሕጉ ለታወጀበት ዓላማ መሳካት የሚያበቃ ትክክለኛ ዕሳቤ ከመመሥረቱ ላይ ይሆናል፡፡

*በሕግ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ነገሮች፡- የኃይልና የዓላማ ሚና*

ሕግጋት የሚታወጁባቸውን ግቦች ማሳካት በሥነ ሕግ ባለው ምደባ ብቻ የሚወሰን አይደለም፤ አንድ ዐዋጅ እንደ ሕግ ተቆጥሮ ተፈጻሚ ቢሆንም እንኳ ግቦቹን ለማሳካት ተፈጻሚና ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ በእጅጉ ወሳኝ ነው፡፡ ለምሳሌ የኢፌዴሪ የወንጀልና የፍትሐ ብሔር ሕግጋትን ብንመለከት ሁለቱም የፍሬነገርና የሥነ ሥርዓት ሕግጋትን አካትተው የያዙ ሲሆኑ፣ ሁለቱም የየራሳቸው ግቦች አሏቸው፡፡ በዚህ መልኩ የሕግጋት መዘጋጀት ከአፈጻጸም ሥነ ሥርዓት ጋር ተያይዘው ሊነሡ የሚችሉ ጥርጣሬዎችንና ጥያቄዎችን ሊያስወግድ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህ ብቸኛው ግብዐት እንዳልሆነው ሁሉ ሥነ ሥርዓቱ አንዴ ከጸደቀ በኋላ በአግባቡ ለመተግበሩ ዋስትና ይሆናል ማለት አይደለም፡፡ ተከታዮቹ ግብዐቶችም ግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል፡- ሕግ የማውጣት ኺደቱ፣ ሕግጋቱን የሚያወጡና የሚያስፈጽሙ ተቋማት፣ አስፈላጊው የገንዘብ አቅርቦት፣ የሠለጠነ የሰው ኃይል እንዲሁም የቁሳቁስ ግብዐት እኩል የአስፈላጊነት ደረጃ ስላላቸው አፈጻጸሙን ሊያስተጓጉሉ ቢችሉም ባይችሉም ተፈላጊውን ውጤት በማግኘት ላይ ግን ግልጽ የሆነ ተጽእኖ መፍጠራቸው አይቀርም፡፡

እንደ ኢትዮጵያ የወንጀልና የፍትሐ ብሔር ሕግጋት ሁሉ የአፍሪካ የሰብዓዊ መብቶች ሥርዓት የተመሠረተው ሰባት ቃል ኪዳኖችን አካትቶ በመያዝ ሲሆን፣ ከእነዚያ ውስጥ የተወሰኑት ዝርዝር የአፈጻጸም ሥርዓት ሲኖራቸው ሌሎቹ ግን ‹ልል ሕግጋት› ናቸው፡፡ ሥርዓቱ የተዘረጋው እ.ኤ.አ በ1969 የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የአፍሪካን የስደተኞች ችግር ለመቅረፍ ያጸደቀውን ቃል ኪዳን በተቀበለው ጊዜ ነበር፡፡ በቅርቡ እንኳ በ2011 ‹‹የዴሞክራሲ፣ የምርጫና የአስተዳደር ቻርተርን›› የአፍሪካ ኅብረት ቢቀበልም ለዐሥርት ዓመታት የዘለቁት እነዚህ ጥረቶች የቀድሞውን የላይቤሪያ ፕሬዚደንት ቻርለስ ቴይለር መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ከመፈጸም፣ የሩዋንዳውን ዕልቂት ከመከሰት ወይም የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የአሁኑ የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫ በሆነችው ኢትዮጵያ በ1970ዎቹ በወታደራዊው ደርግ ለተፈጸሙት አሰቃቂ የሰብዓዊ መበት ጥሰቶች ኃላፊነት ያለባቸውን ለተጠያቂነት በማቅረብ ረገድ ውጤታማ ናቸው ወይ ብለን ብንጠይቅ መልሱ ‹‹አይደለም›› ሆኖ ነው የምናገኘው፡፡ ምናልባት ተስፋ የተጣለበትን ያህል ባይሆንም የቻርለስ ቴይለር ተጠያቂ ሆኖ ለፍርድ መቅረብ እንደ በጎ ጅምር ሊወሰድ ይችላል፡፡ እንዲህም ሆኖ እንኳ የፍርድ አፈጻጸምን በተመለከተ እንደሚነገረው

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ከገጽ 3 የዞረ

## በአፍሪካ ለሚፈጸሙ

ከሆነ ፍርደኛው 50ዓመታትን በብሪታንያ እሥር ቤት ውስጥ የሚያሳልፍ ሲሆን፣ ይህም ግብር ከፋዩን ብሪታንያዊ በየዓመቱ 80ሺህ ፓውንድ ያስወጣዋል፡፡ ለሌሎች ጉዳዮች ካልሆነ በቀር ይህን የሚያህል ከፍተኛ በጀት የአፍሪካ ሐገራት ፍርዱን እዚሁ አሕጉር ውስጥ ተፈጻሚ ለማድረግ ከዐቅማቸው በላይ ይሆንባቸዋል፡፡ ይህ በግልጽ የሚያሳየው የሕግ የበላይነትን ለማስፈን የዐቅም ወይም የፍላጎት ማነሥን ብቻ ሳይሆን የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠንንም ጭምር ነው፡፡ በሌላ በኩል ጉዳዩ የተፈጸመው አፍሪካ ውስጥ ቢሆንም፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰዎችም አፍሪካውያን ቢሆኑም፣ ግንዛቤ የመፍጠር እንዲሁም የሰዎችና የሕዝቦች መብቶችን ቻርተር የማክበሩና የማስከበሩ ኃላፊነት በዋናነት የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን ቢሆንም በጉዳዩ ላይ የመረጃ ምንጮቻችን የውጭ ምንጮች ናቸው፡፡

**ይህ በግልጽ የሚያሳየው የሕግ የበላይነትን ለማስፈን የዐቅም ወይም የፍላጎት ማነሥን ብቻ ሳይሆን የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠንንም ጭምር ነው**

### የማጠቃለያ ሐሳብ

ከሕግ ማዕቀፎቹና አፈጻጸማቸው ጋር በተያያዘ ያሉትን ፈተናዎችና እንቅፋቶች በስፋት መዘርዘሩ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ፈጻሚዎችን ለፍርድ ለማቅረብ የሚደረገውን ጥረት ሊሳካ የማይችል ቢያስመስለውም የአፍሪካ የሰብዓዊ መብቶች ሥርዓት ከነፈተናዎቹ ረዥም ርቀት የተጓዘ ከመሆኑ በላይ የአፍሪካ ሐገራት በሌሎች ሐገራት ጉዳዮች ጣልቃ ያለመግባት ፖሊሲዎቻቸውን በመለወጥ ላይ ከሚገኙበት ዘመን ላይ ደርሰናል፤ ይህም ብቻ ሳይሆን አፍሪካውያን መሪዎች በሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ረገድ የእርስበርስ መገማገሚያ መድረክ መሥርተው ለማየትም በቅተናል፡፡

ስለሆነም፣ መጠነሰፊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የፈጸሙና በመፈጸም ላይ የሚገኙትን በሕግ ተጠያቂ ለማድረግ ከሁሉ አስቀድሞ በመጀመሪያ ከላይ የተጠቀሱትን መልካም ጅምሮች ለማስቀጠል መጣር፣ አሕጉራዊ ጥረቱን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ የማስተዋወቅ ራዕይ ያላቸው የማያወላውል ዐቋም ይይዙ ዘንድ ማሳመን ወሳኝ ነው፡፡

በተለይም ለተከታዮቹ ነጥቦች ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ተገቢ ይሆናል፡- የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽንን በተመለከተ ከቃል ኪዳኑ አንቀጽ 30 አኳያ በሰዎችና በሕዝቦች መብት ዙሪያ የተሻለ ግንዛቤ መፍጠር ብቻ ሳይሆን የኮሚሽኑን የሥልጣን ወሰን በመላው የአፍሪካ ሕዝብ ላይ የሚያርፍ እንዲሆን መጣር ወሳኝ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከቃል ኪዳኑ አንቀጽ 40 አኳያ የኮሚሽኑ አባል ሐገራት ቃል ኪዳኑን ተፈጻሚ የሚያደርጉበትን ሥርዓት ማሻሻል ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

- የአፍሪካ የሰብዓዊ መብቶችና የፍትሕ ፍርድ ቤትን በተመለከተ ልክ እንደ ኮሚሽኑ ሁሉ ተቋኑ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በመከላከል ረገድ ሊያበርክት የሚችለውን ትልቅ አስተዋጽዖ በስፋት ማስተዋወቅ ይገባል፡፡

- እያንዳንዱ በሰላም የሚያልፍ ቀን ያሉትን ውስን ሀብቶች ከማውደም ይልቅ በአግባቡ ለመጠቀም ስለሚያስችል ሰላም ከምንም ነገር በላይ ትልቅ ቦታ ሊሰጠው ይገባል፡፡

- እነዚህንና ሌሎች እርምጃዎችን መውሰድ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለመከላከልና የመብት ጥሰት ፈጻሚዎችን ተጠያቂ ለማድረግ ያስችላል፡፡



# ጽንፈኛ ብሔር ተኮር ፖሊቲካና ያልተመለሱ የማንነት ጥያቄዎች

*የየራሳቸው ባሕልና ቋንቋ ያላቸው የተለያዩ ነገዶች በጋራ በሚኖሩባት ኢትዮጵያ ጽንፈኛ የብሔር ፖሊቲካ የሚጫወተውን አፍራሽ ሚና እንዲሁም የፖሊቲካ ዕሳቤው ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰት መንሥዔ ሊሆን እንደሚችል*

<u>ሱራፍኤል ግርማ</u> *በተከታዩ ጽሑፍ ሊያሳይ ይሞክራል*

ከሰብዓዊነት ዕሳቤ ጋር የሰፋ ተቃርኖ ያለው ጽንፈኛ ብሔር ተኮር ፖሊቲካ በአዳም ልጅነታቸው አንድ የሆኑትን ሰብዓዊ ፍጡራን ‹‹የብሔር አባላትና የብሔር አባላት ያልሆኑ›› በሚል በሁለት ምድብ ከፋፍሎ ለመመልከት ያስገድዳል፡፡ ሰዎች የዓለም ምልከታቸው በጽንፈኛ የብሔር ፖሊቲካ የተቃኘ በሚሆን ጊዜ የሌሎችን ሰውነት በመዘንጋት ለራሳቸው ጎሣ አባላት ማድላታቸው አይቀርም፡፡ ጽንፈኛ ብሔር ተኮር ፖሊቲካ ልዩነትን በማጉላት ጥላቻ እንዲያቆጠቁጥ መንሥዔ ስለሚሆን ብዙኃንን ለአንድ ዓላማ ሊያሰልፍ ካለመቻሉ በላይ የዚህ ፖሊቲካ መሥመር ተከታዮች ከእነርሱ ብሔር ውጭ የሌሎች ብሔሮች አባላትን የማንኳሰስ አባዜ ስለሚጠናወታቸው ለኢ-ፍትሐዊነትና ለኢ-ሞራላዊነት መንሥዔ ይሆናል፡፡

ብሔር ተኮር ፖሊቲካ የሌላውን ብሔር አባላት ሰብዓዊነት ባለመቀበል በግለሰብም ይሁን በማኅበረሰብ ደረጃ የሚፈጸሙ የጥላቻ ወንጀሎችን እንደ ሠናይ ምግባር የሚቆጥር አደገኛ ርዕዮት ነው፡፡ በዕርቅና በይቅርታ ሕዝቡ አብሮ የሚኖርበትን መንገድ ከመፈለግ ይልቅ ላለፉ በደሎች የቂም በቀል የጅምላ የቅጣት እርምጃ ተገቢ መሆኑን ይሰብካል፤ በዚህም ምክንያት የብሔር ተኮር ፖሊቲካ አራማጅ ዓምባ ገነኖች የሚፈጽሟቸው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ሌሎች ዓምባ ገነኖች በሥልጣን ላይ ለመቆየት ሲሉ ከሚፈጽሟቸው በደሎች እጅግ የከፉ ናቸው፡፡

የብሔር ጭቆና ለዘመናት ተንሠራፍቶ መቆየቱን የሚያምነው ኢሕአዴግ ሥልጣን ሲይዝ ይህን ተቃርኖ ለማረም መፍትሔ አድርጎ የወሰደው እርምጃ ብሔር ተኮር በሆነ ፖሊቲካዊ አደረጃጀት የተቃኘ ፌዴራሊዝምን በመሆኑ ከ1983ዓ.ም ወዲህ የዜጎች ግለሰባዊና ሰብዓዊ ማንነት ደብዝዞ የሀብት ክፍፍሉና የተጠቃሚነት ዕድሉ ብሔርን መሠረት ያደረገ ሆኗል፡፡ በዚህም ምክንያት ዛሬ በኢትዮጵያ የአንድ ብሔር ተወላጅ መሆን የየትኛው የፖሊቲካ ፓርቲ አባል የመሆን ዐቋምን የሚወስን ሆኗል፡፡

በመንግሥትም ይሁን በተቃዋሚ ብሔር ተኮር ፓርቲዎች የሚቀነቀነው ብሔር ተኮር ፖሊቲካ በሕገ መንግሥቱ የተከበረውን ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመጻፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግና ባሕሉን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብቱን ይበልጥ በማጎልበት ላይ ያተኮረ ከመሆን ይልቅ በአሉታዊ መንገድ ልዩነትን የሚያጎላና በቂም በቀል መንፈስ የተቃኘ በመሆኑ የሐገራችንን ብሔራዊ አንድነት ሸርሽሮ ከመቼውም ጊዜ በላይ ዜጎች የጎሪጥ መተያየታቸው፣ በብሔር እየተቧደኑ እርስበርስ መቆራቆዛቸው የተለመደ አሳዛኝ ክስተት ሆኗል፡፡

ገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ ጎሣንና ቋንቋን መሠረት ያደረገ

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ከገጽ 5 የዞረ

## ጽንፈኛ ብሔር . . .

የአስተዳደር ሥርዓት በአገሪቱ ካሰፈነበት ጊዜ ጀምሮ በአብዛኞቹ የሐገራችን ክፍሎች ተደጋጋሚ የጎሣና የሃይማኖት ግጭቶች ተከስተዋል፡፡ የኢሰመጉ (ሰመጉ) መግለጫዎች በተጨባጭ እንደሚያሳዩት በአካባቢ ባለሥልጣናትና ፖሊቲከኞች ቀስቃሽነት በተለያዩ ብሔረሰቦች መካከል ግጭቶች ተቀስቅሰው የብዙዎች ሕይወት ጠፍቷል፣ በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎችም ከባድና ቀላል የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ ከፍተኛ ግምት ያለው ንብረትም ለውድመት ተዳርጓል፡፡

በቀድሞው አጠራሩ ኢሰመጉ የአሁኑ ሰመጉ እነዚህን ክስተቶች እየተከታተለ መረጃዎችን በማሰባሰብ በተደጋጋሚ ባወጣቸው መደበኛና ልዩ መግለጫዎች ላይ የችግሩን አሳሳቢነት ሲያስታውቅና ተገቢ መፍትሔ የሚያሻው መሆኑን ሲገልጽ ቆይቷል፡፡ መንግሥትም ሆነ ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ችግሩ እየተስፋፋ እንዳይሄድና ወደ ባሰ እልቂት እንዳያመራ የየበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ ሲያሳስብም ቆይቷል፡፡ ነገር ግን የሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን የመፍትሔ እርምጃ ባለመውሰዳቸው ግጭቶቹ ተባብሰው እንደቀጠሉ ናቸው፡፡

በአሁኑ ሰዓት እየተተገበረ ካለው የፌዴራል ሥርዓት ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ ሲከሰት የሚስተዋለው ሌላው ችግር በአንድ ብሔር ስም በተዋቀሩ ክልሎች የሚኖሩ የሌሎች ብሔሮች ተወላጆች በማንነታቸው ታውቀውና የቡድን መብቶቻቸው ተከብረውላቸው ባሕልና ቋንቋቸውን እንዲያሳድጉ በአጠቃላይ ራሳቸውን በማስተዳደር ለመኖር ለሚያቀርቧቸው የማንነት ጥያቄዎች አጥጋቢ ምላሽ ሳያገኙ መቅረታቸው ነው፡፡ ለአብነት ያህልም በትግራይ ክልል የራያና የወልቃይት ጠገዴ ሕዝቦች፣ በሶማሌ ክልል የሬርባሬና የዱቤ ሕዝቦች እንዲሁም በአማራ ክልል የቅማንት ሕዝብ ያነሷቸው የማንነት ጥያቄዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የኢሕአዴግ መንግሥት ከሚከተለው ብሔር ተኮር ፖሊቲካ የተነሣ የብሔሮች ወኪሎች ተደርገው በሚወሰዱት የክልል መስተዳድሮችና በተለያዩ ብሔሮች መካከል ሰፊ የሀብት ድልድል ልዩነት መኖሩ የፈጠረው ቅሬታ ነው ለዚህ ጥያቄ መነሣት ዋና ምክንያት፡፡

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 ንዑሥ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው፡፡ ይህ መብት ብሔሩ፣ ብሔረሰቡ፣ ሕዝቡ በሠፈረበት መልክዓ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋም እንዲሁም በክልልና በፌደራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል፡፡ በአንጻሩ የማንነት ጥያቄ የሚያነሡ ወገኖች ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር፣ ባሕላቸውንና ቋንቋቸውን ለማሳደግ መጠየቃቸው በየክልሎቹ ገዢዎች እንደወንጀል ተቆጥሮ የብሔረሰቦቹ አባላት ለግድያ፣ ለእሥራት፣ ከሥራ ለመባረርና ለሌሎች የበቀል እርምጃዎች ሰለባ ሲሆኑ ይስተዋላል፡፡ በዚሁ ሳቢያ የሚነሣ ግጭትም ለበርካታ ሰዎች መገደል፣ መቁሰልና ከመኖሪያ መፈናቀል ምክንያት ሆኗል፡፡

የማንነት ጥያቄ የሚያሡ ወገኖች ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው እንዲከበርላቸው የሚያቀርቡት መከራከሪያ ቀድሞውኑ ብሔርን መሠረት ባደረገ ፌደራሊዝም ክልሎች

ወደ ገጽ 7 ዞሯል





ከገጽ 6 የዞረ

## ጽንፈኛ ብሔር . . .

ሲዋቀሩ ሕዝቡ በዕጣ ፈንታው ላይ በአግባቡ እንዲመክርና በራሱ ጉዳይ ላይ እንዲመክር፣ ሐሳቡን በግልጽ ሰጥቶ የውሳኔው አካል እንዲሆን የሚያደርግ ዕድል ሳይሰጠውና ፍላጎቱም ግምት ውስጥ ሳይገባ አካባቢውን በበላይነት ይቆጣጠሩ በነበሩ ኃይሎች ወደ አንዱ ክልል እንዲካለል ተደርጎ በቋንቋው የመዳኘት፣ የመሥራትና የመማር ዕድሉን ተነፍጎ የራሱ ያልሆነ ማንነት እንዲላበስ ለማድረግ ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑን ነው፡፡

**ብዙውን ጊዜ እንደሚስተዋለው ብሔር ተኮር ፖሊቲካ በበቂ ሁኔታ የማይገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን፣ የኢኮኖሚ አውታሮችንና ሥልጣንን በብቸኝነት ለመቆጣጠርና ለመጠቀም ይቻል ዘንድ ጽንፈኞች የሚቀይሱት የረቀቀ ዘዴ ሲሆን፣**

ብዙውን ጊዜ እንደሚስተዋለው ብሔር ተኮር ፖሊቲካ በበቂ ሁኔታ የማይገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን፣ የኢኮኖሚ አውታሮችንና ሥልጣንን በብቸኝነት ለመቆጣጠርና ለመጠቀም ይቻል ዘንድ ጽንፈኞች የሚቀይሱት የረቀቀ ዘዴ ሲሆን፣ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ የሀብት ድልድሉ ብሔርን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በተለያዩ ክልሎች መካከል በትምህርት፣ በጤና አጠባበቅ፣ በምጣኔ ሀብት እንዲሁም በፖሊቲካዊ መስኮች እጅግ የተለያየ ውጤት ሲመዘገብ መስተዋሉ ለዚህ ማሳያ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የማንነት ጥያቄ በተነሣባቸው ክልሎች ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ብሔር ተወላጆች መካከል ያለው ግንኙነት የገዢና የተገዢ፣ የበዝባዥና የተበዝባዥ መሆኑን የሚገልጹ ወገኖች ጥቂት ምሳሌዎችን ነቅሰው በማውጣት ቀድሞውኑ ከሕዝብ ፍላጎት ውጭ ክልሎቹ የተዋቀሩበትን መንገድ ‹‹የአካባቢው ለምነት ባለሥልጣናቱን በጣም ስላጓጓ እንጂ ወደራሳቸው ያካለሉት የሕዝቡን ታሪክ፣ ባሕልና ወግ እንዲሁም እውነተኛ ፍላጎትና ሥነ ልቦናዊ ትሥሥር ተጠንቶ አይደለም የተካለለው፡፡››1 በማለት ይተቻሉ፡፡

በተለያዩ የሐገራችን አካባቢዎች የሚነሡ ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄዎች በሕገ መንግሥቱ አግባብ ሊፈቱ ሲገባቸው እየተንተቱ መጥተው ለዜጎች ሕይወት መጥፋት፣ አካል መጉደል፣ የንብረት ውድመት መንሥዔ መሆናቸው አሳዛኝ ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት የደረሰው ጥፋት በገለልተኛ አጣሪ ቡድን እንዲጣራና ለደረሰው የሕይወት ጥፋት፣ አካል ጉዳትና የንብረት ውድመት ተጠያቂ የሆኑትን ግለሰቦች ለፍርድ እንዲቀርቡ በማድረግ መንግሥት የዜጎችን የሕይወት፣ የአካል ደኅንነትና የንብረት መብቶችና ነጻነቶች በማስጠበቅ በኩል ያለበትን ሕገ መንግሥታዊ ግዴታ በአግባቡ መወጣት ይጠበቅበታል፡፡

*ምንጭ፡- 1.የራያ ሕዝብ የማንነት ጥያቄና የማዕከላዊ መንግሥታት ምላሽ*

# የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ቁርጠኛነት ከፓሪስ መርሖዎች አንፃር

*የተ.መ.ድ አባል ሐገራት የሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር ያላቸው ቁርጠኛነት ከሚመዘንባቸው መሥፈርቶች መካከል ‹‹የፓሪስ መርሖዎች›› ተጠቃሾች ናቸው፤ **ቢንያም አባተ** ከመርሖዎቹ አኳያ የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽንን ወቅታዊ ዐቋም ይፈትሻል፡፡*

በ1992 እ.ኤ.አ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ያገኙ፣ ሐገር አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማትን የሥልጣን ወሰንና የሥራ አፈጻጸም የሚመለከቱ መርሖዎችን አጽድቋል፡፡ ይህንንም ተከትሎ በ1993 እ.ኤ.አ በተ.መ.ድ ጠቅላላ ጉባዔ የጸደቁት ‹‹የፓሪስ መርሖዎች›› አባል ሐገራት ለሚያቋቁሟቸው ሐገር አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተቋማት መሠረታዊ መመሪያዎችን አስቀምጧል፡፡ በተ.መ.ድ ገለጻ መሠረት ሐገር አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማት በሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ወይም በሕግ የሚቋቋሙ የመንግሥት አካላት ሲሆኑ፣ ዋና ተግባራቸውም ለሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ ማድረግና በኀብረተሰቡ ዘንድ ያለውን ግንዛቤ ለማዳበር ማስተዋወቅ ነው፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሐገር አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማትን በሦስት ምድብ ይከፍላቸዋል፡- የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽኖች፣ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋማት እንዲሁም ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የኀብረተሰብ ክፍሎችን (አናሳ ጎሳዎችን፣ የአንድ አካባቢ ቀደምት ነዋሪዎችን፣ ስደተኞችን፣ ሴቶችን ወይም ሕፃናትን) መብቶች ለማስከበር የሚቋቋሙ ልዩ ተቋማት ናቸው፡፡

የፓሪስ መርሖዎች በተከታዮቹ ነጥቦች ላይ አጽንኦት ይሰጣሉ፡-

1. ሐገር አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማቱ በሕገ መንግሥታዊ ወይም ሕጋዊ መሠረት ላይ እንዲታነጹ፣
2. በተቻለ መጠን ሰፊ የሥልጣን ወሰን እንዲኖራቸው፣
3. ገለልተኛነትን የተላበሰ የሹመት መመሪያ እንዲኖርና የተቋማቱ መሪዎች የሥራ ዘመን በሕግ የተወሰነ እንዲሆን፣
4. ብዝኃነት እና የተሟላ ውክልና ያለው ጥንቅር እንዲኖራቸው፣
5. መደበኛና ውጤታማ አሠራር የሰፈነባቸው እንዲሆኑ፣
6. ከመንግሥት ሥራ አስፈጻሚ አካላት ገለልተኛ እንዲሆኑና
7. በቂ በጀት ኖሯቸው እ ን ዲ ን ቀ ሳ ቀ ሱ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሐገር አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማት የሥራ አፈጻጸምን በተመለከተ የፓሪስ መርሖዎች መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮችን በራሳቸው ተነሣሽነት፣ በመንግሥት አካላት ጥቆማ እንዲሁም በማንኛውም አቤቱታ አቅራቢ ጥያቄ መሠረት መከታተል የሚችሉ ተቋማትን መፍጠር እንደሚኖርባቸው ያሳስባሉ፡፡

8. ሐገር አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማት በሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ ለመንግሥት ሪፖርትና ምክረ ሐሳብ ማቅረብ (የሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር የሚያስችሉ

ወደ ገጽ 9 ዞሯል



ከገጽ 8 የዞረ

## የሰብዓዊ መብት . . .

ሕግጋት እንዲወጡ፣ ዓለም አቀፍ ሕግጋት ተቀባይነት አግኝተው እንዲጸድቁ መወትወት እንዲሁም በሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ መግለጫዎችንማውጣት) ይጠበቅባቸዋል፡፡

9. በሐገር አቀፍ ደረጃ የሚወጡ ሕግጋትና ተግባራት ከዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መሥፈርቶች ጋር የሚጣጣሙ እንዲሆኑና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ቃል ኪዳኖችን መንግሥታት እንዲያጸድቁ መወትወት፣
10. ለ ተ ባ በ ሩ ት መንግሥታት ድርጅት አካላትና ኮሚቴዎች በሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ አስተዋጽኦ ማበርከትን ጨምሮ ከሌሎች ሐገር አቀፍ፣ አካባቢያዊና ከተ.መ.ድ የሰብዓዊ መብቶች አካላት ጋር መተባበር፣
11. በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ ትምህርት መስጠት እንደሚኖርባቸው በፓሪስ መርሖዎች በአጽንኦት ተገልጿል፡፡

ከሁሉ በላይ፣ በመንግሥታት የሚቋቋሙ ሐገር አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማት በተለይም የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽኖች ሥራዎቻቸውን በቀጥታ ወይም በብዙኃን መገናኛ አማካይነት ለሕዝብ ይፋ ለማድረግ ብቁ ሆነው መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡

የፓሪስ መርሖዎች የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽኖች ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ከቆሙ ሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበርና በመመካከር እንዲሠሩ መመሪያ ያስቀምጣሉ፡፡ መንግሥታዊ ካልሆኑ የሰብዓዊ መብት ተቋማት፣ ከሙያ ማኅበራት፣ ከታዋቂ ተመራማሪዎች፣ ከፈላስፎችና ምሁራን፣ ከሃይማኖት መሪዎች ጋር ወዘተ ተባብሮ መሥራት አስፈላጊ መሆኑ ላይ መርሖዎቹ ያሠምሩበታል፡፡

የፓሪስ መርሖዎች በመርሕ ደረጃ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር መልካም ጅምር ሆነው ሳለ ያሉባቸው ውሱንነቶች በደንብ የሚንጸባረቁት በየሐገራቱ መንግሥታት የሚያቋቁሟቸውን የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽኖች እንቅስቃሴዎች በመመርመር ነው፡፡ የፓሪስ መርሖዎችን ተቀብሎ ማጽደቅ የሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ቢሆንም የሰብዓዊ መብቶች መከበርን እውን ለማድረግ ቁርጠኛ የሆኑ፣ ከሌሎች የመንግሥት አካላት ተቃውሞ ሲገጥማቸው በዐቋማቸው የሚጸኑ ኮሚሽነሮች የሚመሯቸው ኮሚሽኖች ካልተቋቋሙ በቀር መርሖዎቹም የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎቹም ከወረቀት ፍጆታ ያለፈ ፋይዳ አይኖራቸውም፡፡

በዚሁ መንፈስ መሠረት መንግሥታት በየሃገራቸው የሚፈጸሙ ጥሰቶችን ለመከላከል፤ ተፈጽመውም ሲገኙ ለማጣራትና ለማጋለጥ፤ እንዲሁም የዜጎችን የሰብዓዊ መብት ግንዛቤ ለማዳበር የሰብዓዊ መብት ተከላካይና ተንከባካቢ ተቋማትን ያቋቁማሉ፡፡ እንደ ሌሎች መንግስታት ሁሉ የኢትዮጵያ መንግሥትም ለተመሳሳይ ዓላማ "የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን"ን በ1992 ዓ ም አቋቁሟል፡፡

በኮሚሽኑ የማቋቋሚያ ዐዋጅ ቁጥር 210/1992 መሠረት የኮሚሽኑ ዓላማ ስለ ሰብዓዊ መብቶች ግንዛቤ ከማስጨበጥ ጀምሮ በመብት ጥሰት ፈጻሚዎች ላይ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ እስከማድረግ ይደርሳል፡፡ ኮሚሽኑ ዐሥራ አምስት ዓመታትን በዘለለው የሥራ ዘመኑ በሐገራችን ለሰብዓዊ መብቶች መከበር፤ ጥበቃና ግንዛቤ ማስጨበጫ ያደረገው አስተዋጽዖ ከመሠረታዊ ዓላማውና ከ"ፓሪስ መርሆች" አንጻር ሊመዘን ይገባዋል፡፡ በ"ፓሪስ መርሖች"

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

ከገጽ 9 የዞረ

## የሰብዓዊ መብት . . .

መሠረት ሐገር በቀል የሰብዓዊ መብት ተከላካይና ተንከባካቢ ተቋማት ከማንኛውም አካል በተለይም ከመንግሥት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖሊቲካዊና አስተዳደራዊ ተጽዕኖና ጥገኝነት የተላቀቁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የተቋማቱ አመሠራረት የተለያዩ የኅብረተሰብ አካላትን በማማከል ብዝኃነትን ያስከበረ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ዓለም አቀፍ መርሖዎች የአንድን የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ ነጻነት፣ ከወገንተኛነት የጸዳ አወቃቀርና ድርጅታዊ ዐቋም መመዘኛ ነጥቦቻችን ናቸው፡፡ በተያያዘም እነዚህ ነጥቦች የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶችን የሥራ ውጤታማነት አመላካቾች ናቸው፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በግንቦት ወር 1990ዓ.ም የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንን ለመመሥረት በጠራው ‹‹የሰብዓዊ መብቶች ኮንፍረንስ›› ከ68 ሐገራት የተውጣጡ ተወካዮችን ቢጋብዝም በኢትዮጵያ መንግሥት የሰብዓዊ መብት አያያዝ ላይ ጠንካራ አስተያየት በመስጠት የሚታወቁትን አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ ሂውማን ራይትስ ዎች፣ ሂውማን ራይትስ ሊግ እንዲሁም ሐገር በቀል የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችን የጉባዔው ተካፋይ እንዲሆኑ አለመፍቀዱ ከመነሻው የኮሚሽኑን ገለልተኛነት ጥያቄ ውስጥ ማስገባቱ ይታወሳል፡፡

ከፓሪስ መርሖዎች መካከል በዋነናነት ሊጠቀስ የሚገባው መመዘኛ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ሊሰጣቸው የሚገባው የሰፋ ሥልጣንና ተግባር ነው፡ ፡ በዐዋጅ ቁጥር 210/1992 አንቀጽ 6 መሠረት ኮሚሽኑ የሰብዓዊ መብቶች ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት የተደነገጉት ሰብዓዊ መብቶች በማንኛውም አካል መከበራቸውን ማረጋገጥ፣ መንግሥት የሚወጡ ሕግጋት ከሰብዓዊ መብቶች ጋር አለመቃረናቸውን ማረጋገጥ፣ በራሱ ተነሣሽነትም ሆነ በሚደርሰው ጥቆማ መሠረት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ማጣራት ይገኙበታል፡፡

ይሁን እንጂ ኮሚሽኑ በነጻ ጋዜጠኞችና የፖሊቲካ ተቃዋሚዎች እሥራት ጉዳይ በስፋት በሚነገረው ኢ ሰብዓዊ የሆነ የእሥር ቤቶች አያያዝ ሁኔታዎች ዝምታን መምረጡ እንዲሁም ጥቆማዎችን ለማጣራት የሚያሳየው የተነሣሽነት ችግር ‹‹ቆሜለታለሁ›› ከሚለው ዓላማ ጋር የሚጣረስ ነው፡፡

በተጨማሪም ከልማት ጋር በተያያዘ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የሐገራችን ክፍሎች በዜጎች ላይ የሚፈጸሙ የማፈናቀል ተግባራትናየሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ከማጣራትና መንግሥትን ከመውቀስ ራሱን መቆጠቡ የገለልተኛነቱን ርቀት ብቻ ሳይሆን የሥራ ውጤታማነቱንም የሚያመለክት ነው፡፡ ብዙዎች እንደሚስማሙበት ኮሚሽኑ በመንግሥት ላይ ያለው ኢኮኖሚያዊ፣ አስተዳደራዊም ሆነ ፖሊቲካዊ ጥገኛነት የተቋሙን ውጤት አልባነት የማያስገርም አደርጎታል፡፡ ምንም እንኳ ኮሚሽኑ ራሱን ችሎ ነጻ የሆነ የሕግ ሰውነት ይዞ በዐዋጅ ቁጥር 210/1992 መሠረት ቢቋቋምም በተግባር የሚታየው ግን የኮሚሽኑ ተሿ_ሚዎች የፖሊቲካ ወገንተተኛነት በሕዝብ ዘንድ ተዐማኒነት እንዳይኖረው አድርጎታል፡፡ በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽ ምክር ቤቶች የሚታየው የአንድ ፓርቲ የበላይነት ከሕዝብ በታክስ መልክ ተሰብስቦ በገዢው ፓርቲ በሚቆረጥለት በጀት የሚተዳደር አንድ አካል በራሱ በመንግሥት የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ለማጋለጥ ዐቅምም ሆነ ቁርጠኛነት ይኖረዋል ብሎ መጠበቅ የዋሕነት ይሆናል፡፡



# የመርማሪዎቹ ውሎ

*የአዲስ አበባ ከተማና የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላን ዕቅድን ባለመቀበል በኦሮሚያ ክልል በርካታ ሥፍራዎች ሕዝባዊ የተቃውሞ ሰልፍ ከመደረጉ ጋር ተያይዞ በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በተወሰደ ከመጠን ያለፈ እርምጃ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለማጣራት ወደተለያዩ አካባቢዎች የተሠማሩ የምርመራ ባለሙያዎችን ገጠመኝ* ***ደረጀ መላኩ*** *እንደሚከተለው ያስቃኘናል፡፡*

የሰመጉ መለያውና ግንባር ቀደም ተግባሩ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝና ሁኔታ መከታተል፣ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ማጣራትና በማስረጃ የተደገፉ መግለጫዎችን ማውጣት ነው፡፡ ሰመጉ በሚያወጣቸው መግለጫዎች ሁሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕና ካሣ እንዲያገኙ፣ የመብት ጥሰት ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁና ወንጀል ሠርቶ በነጻ መሄድ እንዲያበቃ፣ ከእያንዳንዱ ክስተት ትምህርት ተወስዶ ለወደፊቱ ጥንቃቄና እርማት እንዲደረግ ሲጮኽና ሲጠይቅ ቆይቷል፣ አሁንም በመጠየቅ ላይ ነው፤ ለወደፊትም በዚሁ ይቀጥላል፡፡

የሰመጉ መበደኛና ልዩ መግለጫዎች ይፋ ለመሆን የሚበቁት የምርመራ ባለሙያዎች በሥራቸው ወቅት የሚገጥሟቸውን እጅግ ፈታኝ የሆኑ ችግሮችን ተጋፍጠው የሚያሰባስቧቸውን ተጨባጭ ማስረጃዎች በማጠናቀር መሆኑ ይታወቃል፡፡ በቅርቡም ከኅዳር ወር መጨረሻ አንሥቶ የአዲስ አበባንና የፊንፊኔ ዙሪያ የተቀናጀ ማስተር ፕላንን በመቃወም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ በሚገኙ በርካታ ከተሞች እና የገጠር መንደሮች ውስጥ ከተቀሰቀሰው ሕዝባዊ ዐመጽ ጋር በተያያዘ የደረሰውን መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ለማጣራት የሰመጉ የምርመራ ባለሙያዎች በበርካታ ሥፍራዎች ተሠማርተው ነበር፡፡

የሰብዓዊ መብት ታጋዮቹ ‹‹ዓመት በዓልን እንኳ ከቤተሰብ ጋር ሳክበር›› ሳይሉ የሙያ ግዴታቸውን ለመወጣት በሄዱባቸው አካባቢዎች በርካታ መሰናክሎች አጋጥመዋቸዋል፡ ፡ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ለማጣራት ወደ አንድ ሥፍራ ጉዞ ሲጀመር አካባቢውንና ነዋሪውን በደንብ የሚያውቅ ሰው (contact person) ማግኘት ለመርማሪዎቻችን የመስክ ሥራ ስኬት ወሳኝ ነው፡፡ ከጥር ወር መጀመሪያ አንሥቶ በኦሮሚያ ክልል ወደሚገኙ የተለያዩ ሥፍራዎች የተንቀሳቀሱ መርማሪዎቻችን በመስክ ቆይታቸው ከገጠሟቸው ችግሮች መካከል አንዱ በተሠማሩባቸው አካባቢዎች መንገድ ሊመሯቸው፣ ከተጎጂዎችና ከተጎጂ ቤተሰቦች ጋር ሊያገናኟቸው የሚችሉ ሰዎችን አለማግኘት ነበር፡ ፡ ሆኖም ግን ‹‹በተሠማራንበት ሥፍራ የምናውቀው ሰው የለም›› በሚል ምክንያት መስክ የተወጣበትን ሥራ ትቶ መመለስ የማይታሰብ በመሆኑ ባለሙያዎቹ ሥራቸውን በተሳካ ኹኔታ ለማከናወን የሚችሉትን ያህል ጥረዋል፤ አማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎችንም ወስደዋል፡፡ በደምቢ ዶሎ ከተማ በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች የተፈጸመውን አሠቃቂ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ለማጣራት በአካባቢው ተሠማርተው የነበሩ ባልደረቦቻችን ከላይ የቀረበውን ዓይነት ችግር ገጥሟቸው የወሰዱት የመፍትሔ እርምጃ ለዚህ አብነት ይሆናል፡፡

ባልደረቦቻችን የምርመራ ሥራቸውን ለማከናወን በሄዱበት ከተማ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ከደረሰባቸው ሰዎች አንዱ የባጃጅ ሹፌር መሆኑን ቀደም ብለው ካሰባሰቡት መረጃ በማወቃቸው አንዱን የባጃጅ ሹፌር ከነበሩበት ቦታ ወደሌላ አካባቢ እንዲወስዳቸው ተነጋግረው ለአካባቢው እንግዳ መሆናቸውን ተመልክቶ የቆለለባቸውን ከፍተኛ ክፍያ ለመፈጸም ተስማምተው በባጃጁ ይሣፈራሉ፡፡ በጉዟቸው መሐል ከሹፌሩ ጋር ትውውቅ አድርገው ጨዋታ ከጀመሩ በኋላ ሁሉም የባጃጅ ሹፌሮች ሊተዋወቁ እንደሚችሉ በመገመት በዚያ ከተማ ውስጥ ባለፈው ሳምንት ሰላማዊ ሰልፍ መደረጉን ተከትሎ የጸጥታ ኃይሎች በተኮሱት ጥይት ጉዳት የደረሰበት የባጃጅ ሹፌር አድራሻ የት እንደሆነ ሲጠይቁት ለጊዜው ያ የባጃጅ ሹፌር ጓደኛቸውን ማግኘት እንደማይቻል ገልጾላቸው የሌላ ተጎጂንና የአንድ ሟች ቤተሰቦችን መኖሪያ ሊያሳያቸው ፈቅዶ ወደዚያው በመውሰድ ለሥራቸው ስኬት ትብብር አድርጎላቸዋል፡፡ በዚህ መልኩ እንዲሁ ‹‹የዓይን ውኃቸውን›› ዐይተው ካመኗቸው ሰዎች ጋር እዚያው በዚያው ትውውቅ በመፍጠር የሟቾች ቤተሰቦችን፣ ተጎጂዎችንና የተጎጂዎች ቤተሰቦችን አነጋግረው

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

ከገጽ 11 የዞረ

# የመርማሪዎቹ ማስታወሻ . . .

ለሪፖርት የሚበቁ ማስረጃዎችን አሰባስበው በሰላም ተመልሰዋል።

በምዕራብ ሸዋ ዞን ወደምትገኝ አንዲት ከተማ በመሄድ የምርመራ ሥራ እንዲያከናውን የተላከ የመርማሪዎች ቡድን አባላትም ተመሳሳይ ችግር ገጥሟቸው ፈታኙን ሹኔታ በሚከተለው መንገድ አልፈውታል። የቡድኑ አባላት ወደተላኩበት ሥፍራ እንደደረሱ አገናኝ ሰው በሌለበት ሁኔታ መሥራት የሚያስችሉ ሁኔታዎች የትኞቹ እንደሆኑ ለይተው ለማወቅ በሰከነ መንፈስ በመወያየት በዕምነት ተቋማትና በጤና ተቋማት የሚገኙ ሰዎችን እንደ መረጃ ምንጭ ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ወሰኑ፡ ፡ ሆኖም ባሰቡት ልክ ሥራቸው ስላልተቃናላቸው ሌላ አማራጭ መፈለግ ነበረባቸው። ለተመሳሳይ ጉዳይ ወደሌላ አካባቢ ለመስክ ሥራ የወጡ ባልደረቦቻቸው ዘንድ ምክር ፍለጋ ስልክ ሲደውሉ የአጋጣሚ ነገር ሆኖ ከደወሉላቸው ባልደረባችን አንዱ የዚያ ከተማ ነዋሪ የሆኑ ሰዎችን ያውቅ ነበርና ከእነርሱ ጋር በስልክ አገናኝቷቸው ነገሮች መሥመር እንዲይዙላቸው በማድረግ ለጋራ ዓላማቸው መሳካት እገዛውን አበርክቷል።

ሰመጉ ሕጋዊ ሰውነት ኖሮት የሚንቀሳቀስ ተቋም ቢሆንም ብዙ ጊዜ የመንግሥት ሹመኞችም ሆኑ የጸጥታ ኃይሎች ለመርማሪዎች ድጋፍ ማድረግ ቀርቶ የሥራ እንቅስቃሴአቸውን ለማደናቀፍ ሕገ ወጥ ክትትልና ወከባ ማድረጋቸው የተለመደ ነው። በታጣቂዎችና ‹‹ሲቪል›› በለበሱ የጸጥታ እና የደኅንነት ኃይሎች በተወረረ አካባቢ ውስጥ የግድ ሥራቸውን ማከናወን የነበረባቸው የምርመራ ባለሙያዎቻችን ገበያ እንደወጣ ሰው ዘንቢል ገዝተው በመያዝ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር ተመሳስለው የተላኩበትን ግዳጅ ፈጽመው በሰላም የተመለሱበት አጋጣሚም የሚጠቀስ ነው።

የሰመጉ የምርመራ ባለሙያዎች ለሥራ በሚሠማሩበት ወቅት የሚገጥማቸው ችግር በመንግሥት አካላት የሚደረግባቸው ሕገ ወጥ ክትትል ብቻ ሳይሆን በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በተፈጸመባቸው አካባቢዎች ነዋሪዎች የሆኑ ዜጎች ከደረሰባቸው ጉዳት የተነሣ ‹‹ፀጉረ ልውጦችን›› ለማመን ስለሚቸግራቸው መረጃ በመስጠት በኩል በቶሎ አለመተባበራቸውም ጭምር ነው። ሆኖም ግን ሰመጉ ገለልተኛ አጣሪ መሆኑን ሕዝቡ ሲረዳ ልባዊ ዕርዳታ በማድረግ ለሥራው መሳካት አስተዋጽዖ ያበረክታል። ከከተማ ርቀው በሚገኙ ገጠር መንደሮች የተንቀሳቃሽ ስልክ ኔትዎርክ ሽፋን አለመኖሩም በመስክ ሥራ ላይ ብዙ ጊዜ የሚያጋጥም ሌላ እንቅፋት ነው።

የምርመራ ባለሙያዎቻችን ተዘዋውረው የሰብዓዊ መብት ጥሰት ማጣራት ባከናወኑባቸው ሥፍራዎች የመከላከያ ሠራዊት አባላትና የፖሊስ ባልደረቦች በብዛት ይገኙ የነበረ ቢሆንም በጊንጪ ሠፍሮ ከነበረው የጦር ሠራዊት ብዛት የሚበልጥ በሌሎች ሥፍራዎች አለመመልከታቸውን ይናገራሉ፡ ፡ ምንም እንኳ በከተማዋ ውስጥ መሣሪያ አንግተው የሚንቀሳቀሱ ወታደሮችና የፌዴራል ፖሊስ አባላት ብዛት በራሱ የሚያሸብር የነበረ ቢሆንም ሕዝቡ በዚህ ሳይደናገጥ በመንግሥት አካላት የተፈጸመውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት በግልጽ የሚያሳይ ማስረጃ በመስጠት መተባበሩን መርማሪዎቻችን በአድናቆት ይገልጻሉ።

‹‹እኔስ ሰው አማረኝ››

በጽናት የቆመ አምናና ካቻምና፣

ሆኖ የተገኘ ያለፈ ፈተና።

ፍቅርና ትሕትናን አንድ አድርጎ የያዘ፣

በፖለቲካ ተንኮል ልቡ ያልናወዘ።

ሰብዓዊነትን በተግባር የሚያሳየኝ፣

እርሱ ተቆጥቦ አታድርግ የሚለኝ።

ራሱ ተምሮ ለሌላው የሚመክር፣

እኔስ ሰው አማረኝ እውነተኛ መምህር።

አንደበቱ ያማረ ከተንኮል ከሐሜት፣

ልቡናው የነጻ ከክሕደት ከትዕቢት።

እውነተኛ ሆኖ መንገድ የሚመራኝ

የሰመጉ ጀግና እኔስ ሰው አማረኝ።

*ጊታሁን ለዳነ (ከሰመጉ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና ሥራ አመራር)*